412/2013

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No. ሪ/ሲ/ኮ130/ጠማ2/40/182

ቀን/ Date 08 ታህሳስ 2012

"ሠላምና ጤና ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ይሁን!"

በዝርዝሩ ለተመለከቱት

<u>በያሉበት</u>

በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 59 መሠረት ሰራተኞች በስራ ላይ ሳሉ ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ተሰጥቶበት እንደነበር ይታወሳል፡፡

የተሰጡትን አስተያየቶች በማካተት ማስተካከያ የተደረገበትን የስራ ላይ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

ግልባጭ፡-

- ለአደረጃጀት ስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ህጎች፣ ጥናትና ትግበራ ስርፀት ዳይሬክቶሬት
- የሰው ሀብት አዲት ዳይሬክቶሬት

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ስልክ/Tel: +251 115 54 96 66/67
ፋክስ/Fax: +251 115 54 97 07
ፖ.ሳ.ቁ. 1082
Email: contactus@ecsc.gov.et
Website:- www.csc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

መስከረም 2012 ዓ.ም

# የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የተቋሙ ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 1. | ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 2. | ለፌዴሬሽን ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| 3. | ለህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 4. | ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| 5. | ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 6. | ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም | አዲስ አበባ |
| 7. | ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 8. | ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት | አዲስ አበባ |
| 9. | ለብሮድካስት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 10. | ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት | አዲስ አበባ |
| 11. | ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 12. | ለፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 13. | ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 14. | ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 15. | ለሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 16. | ለመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 17. | ለኢትዮጵያ ክይዘን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 18. | ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 19. | ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 20. | ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 21. | ለኢትዮጵያ ብዝሃ-ህይወት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 22. | ለኢትዮጵያ የአካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 23. | ለሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 24. | ለቱሪዝም ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |
| 25. | ለቤተ መንግሥት አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 26. | ለሰላም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 27. | ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 28. | ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 29. | ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 30. | ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 31. | ለብሔራዊ የመረጃ ደህንነት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 32. | ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 33. | ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን | አዲስ አበባ |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

ኮሚሽነር

| | | |
|---|---|---|
| 34. | ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 35. | ለዕርቀ ሰላም ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 36. | ለአስተዳደር ጉዳዮች፣ የወሰንና ማንነት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 37. | ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 38. | ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 39. | ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 40. | ለዲያስፖራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 41. | ለገንዘብ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 42. | ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 43. | ለኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 44. | ለመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 45. | ለመንግሥት ግገርና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 46. | ለጠቅላይ ዓቃቤ ህግ | አዲስ አበባ |
| 47. | ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 48. | ለጠቅላይ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 49. | ለከፍተኛ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 50. | ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 51. | ለጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 52. | ለኢትዮጵያ እእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 53. | ለፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 54. | ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 55. | ለፍትህና የሕግ ምርምርና ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 56. | ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 57. | ለሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 58. | ለግብርና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 59. | ለኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 60. | ለግብርና ምርምር ካውንስል ሴክሬታሪያት | አዲስ አበባ |
| 61. | ለህብረት ሥራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 62. | ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 63. | ለቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 64. | ለእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 65. | ለብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል | ሰበታ |



በዛብሁ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

| | | |
|---|---|---|
| 66. | ለብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 67. | ለብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 68. | ለሚዛን የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሊጅ | ሚዛን |
| 69. | ለአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሊጅ | አጋርፋ |
| 70. | ለአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አላጌ |
| 71. | ለአርጻይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሊጅ | አርጻይታ |
| 72. | ለገዋኔ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሊጅ | ገዋኔ |
| 73. | ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 74. | ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 75. | ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 76. | ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 77. | ለምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 78. | ለኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 79. | ለስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | ደብረ ዘይት |
| 80. | ለፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 81. | ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 82. | ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 83. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 84. | ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 85. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 86. | ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 87. | ለኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 88. | ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 89. | ለኢትዮጵያ ባዩቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 90. | ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 91. | ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 92. | ለትራንስፖርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 93. | ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |



በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

| | | |
|---|---|---|
| 94. | ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 95. | ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 96. | ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 97. | ለመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 98. | ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 99. | ለከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 100. | ለፌዴራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 101. | ለፌዴራል ከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 102. | ለፌዴራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 103. | ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 104. | ለኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 105. | ለውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 106. | ለመስኖ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 107. | ለውሃ ልማት ፈንድ | አዲስ አበባ |
| 108. | ለውሃ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 109. | ለተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 110. | ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ም/ቤት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 111. | ለውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 112. | ለብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 113. | ለኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 114. | ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 115. | ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | አዲስ አበባ |
| 116. | ለትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 117. | ለሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 118. | ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 119. | ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 120. | ለአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 121. | ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዳማ |
| 122. | ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | አዲስ አበባ |
| 123. | ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ | ነቀምቴ |



በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

| | | |
|---|---|---|
| 124. | ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ | ድሬዳዋ |
| 125. | ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ | ደብረብርሃን |
| 126. | ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ | ሮቤ |
| 127. | ለመቐሌ ዩኒቨርሲቲ | መቐሌ |
| 128. | ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ | ሚዛን |
| 129. | ለጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ | ጅግጅጋ |
| 130. | ለአክሱም ዩኒቨርስቲ | አክሱም |
| 131. | ለሰመራ ዩኒቨርስቲ | ሰመራ |
| 132. | ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | ደብረማርቆስ |
| 133. | ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ | አምቦ |
| 134. | ለጅማ ዩኒቨርሲቲ | ጅማ |
| 135. | ለአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ | አርባ ምንጭ |
| 136. | ለሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ | ሀሮማያ |
| 137. | ለዲላ ዩኒቨርሲቲ | ዲላ |
| 138. | ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ | ጎንደር |
| 139. | ለሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ | ሃዋሳ |
| 140. | ለወሎ ዩኒቨርሲቲ | ወሎ |
| 141. | ለመቱ ዩኒቨርሲቲ | መቱ |
| 142. | ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ | አዲግራት |
| 143. | ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ | ቡሌ ሆራ |
| 144. | ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ | ወልቂጤ |
| 145. | ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ | አሶሳ |
| 146. | ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ | ሶዶ |
| 147. | ለወልዲያ ዩኒቨርሲተ | ወልዲያ |
| 148. | ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ | ባህር ዳር |
| 149. | ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ | ደብረ ታቦር |
| 150. | ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ | ጋምቤላ |
| 151. | ለአርሲ ዩኒቨርስቲ | አርሲ |
| 152. | ለዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ | ሆሳዕና |
| 153. | ለወራቤ ዩኒቨርስቲ | ወራቤ |
| 154. | ለቦንጋ ዩኒቨርስተ | ቦንጋ |
| 155. | ለመቅደላ ዩኒቨርስቲ | መቅደላ |
| 156. | ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ | ደባርቅ |
| 157. | ለደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ | ደንቢዶሎ |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

| | | |
|---|---|---|
| 158. | ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ | እንጅባራ |
| 159. | ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ | ሁሮ |
| 160. | ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ | ፍቼ |
| 161. | ለራያ ዩኒቨርስቲ | ራያ |
| 162. | ለጂንካ ዩኒቨርስቲ | ጂንካ |
| 163. | ለቀብሪደሀር ዩኒቨርስቲ | ቀብሪደሃር |
| 164. | ለከፍተኛ ትምህርት አግባቡነትና ጥራት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 165. | ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 166. | ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 167. | ለጤና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 168. | ለቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 169. | ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊንየም ሜዲካል ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 170. | ለአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 171. | ለፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 172. | ለመላ አፍሪካ ስጋ ደዌ መከላከያና ትምህርት መስጫ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 173. | ለአቤት ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 174. | ለገፈርሳ የአዕምሮ ህሙማን ማገገሚያ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 175. | ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 176. | ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 177. | ለመድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 178. | ለኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 179. | ለብሄራዊ የደም ባንክ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 180. | ለአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 181. | ለብሔራዊ የኤች አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 182. | ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 183. | ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 184. | ለኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 185. | ለኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 186. | ለአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 187. | ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻህፍት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 188. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | አዲስ አበባ |



ከተበህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

| | | |
|---|---|---|
| 189. | ለሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 190. | ለስፖርት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 191. | ለገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 192. | ለጉምሩክ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 193. | ለብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 194. | ለፕላንና ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 195. | ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 196. | ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 197. | ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 198. | ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 199. | ለግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 200. | ለኦሮሚያብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 201. | ለአማራ ብ/ክ/መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ | ባህርዳር |
| 202. | ለደቡብብ/ብ/ህ/ብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት<br>ልማት ቢሮ | ሀዋሳ |
| 203. | ለትግራይብ/ክ/መንግስትሲቪል ሰርቪስ ቢሮ | መቐሌ |
| 204. | ለአዲስአበባከተማአስተዳደርፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት<br>ልማት ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 205. | ለድሬዳዋከተማአስተዳደርፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | ድሬዳዋ |
| 206. | ለሐረሪብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | ሐረሪ |
| 207. | ለሶማሌብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | ጅግጂጋ |
| 208. | ለአፋርብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | ሰመራ |
| 209. | ለጋምቤላብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት<br>ቢሮ | ጋምቤላ |
| 210. | ለቤኒሻንጉልጉሙዝብ/ክ/መንግስትፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት<br>ልማት ቢሮ | አሶሳ |

ብዙነህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

FDRE CIVIL SERVICE COMMISSION

# የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች በስራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል መመሪያ

# 412/2013

ታህሳስ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች በስራ ላይ ሳሉ ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "አዋጅ›› ማለት የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው፡፡
2. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤
3. "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡
4. "ጊዜያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባሕርይ በሌለው ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው፤
5. "የሥራ ሁኔታ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ያለ ጠቅላላ የሥራ ግንኙነት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ልዩ ልዩ ፈቃዶችን፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነትን፣ የሠራተኞች የሥራ ስንብት ሁኔታና ክፍያ፣ የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቶችን እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
6. "የህክምና ወጪ" ማለት አንድ የመንግስት ሰራተኛ ከስራ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት ለሀገር ውስጥ ህክምና የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡
7. ‹‹በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት›› ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

ሙፈሪሀት ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

8. ‹‹በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

9. ‹‹በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ›› ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ወይም በሽታዎችን በማጥፋት ስራ ተሰማርቶ እያለ ባለበት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን፣ ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና ስር የሰደዱ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡

10. ‹‹የአካል ጉዳት›› ማለት የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

11. ‹‹ጊዜያዊ የአካል ጉዳት›› ማለት ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የመሥራት ችሎታን ማጣት ነው፡፡

12. ‹‹ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት›› ማለት የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

13. ‹‹ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት›› ማለት ጉዳት የደረሰበትን የመንግሥት ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

14. ‹‹የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች›› ማለት በስራ ቦታ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ለመከላከል የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡፡

15. "የህክምና ተቋም" ማለት በሀገር ውስጥ አግባብ ባለው ባለስልጣን ፍቃድ የተሰጠው የመንግስት ወይም የግል የህክምና ተቋም ነው፡፡

3. የጾታ አገላለጽ፣

በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2 የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ሰራተኛ እና ጊዜያዊ ሰራተኛ በሚል ትርጉም በሚሸፈኑ ሰራተኞችና መስሪያ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 5. የመመሪያው ዓላማ

በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ ላይ አደጋ ስጋቶችን፣ በሥራ ምክንያት በሰራተኛው ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመከላከል እና ጉዳት ሲደርስም ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ ወጪውን በመሸፈን የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነትን መፍጠር ነው።

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

## ክፍል ሁለት

### 6. በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎች የህክምና ወጪ አከፋፈል

1. በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ሠራተኛ በሀገር ውስጥ በሚገኝ የመንግስት የሕክምና ተቋም ህክምናውን ተከታትሎ የህክምና ማስረጃ ካቀረበ በአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለሚከተሉት የሕክምና አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ወጪ በመሥሪያ ቤቱ ይሸፈናል፡፡
   1) የጠቅላላና የልዩ ሕክምና፤
   2) የቀዶ ሕክምና፤
   3) የሆስፒታልና የመድኃኒት፤
   4) የማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሰራሽ ምትክ ወይም ተጨማሪ አካሎችና የአጥንት ጥገና ወጪዎች፡፡
2. ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ የህክምና አገልግሎት በግል የህክምና ተቋም እንዲሰጠው የሚደረገው በአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አገልግሎቱ በመንግሥት የሕክምና ተቋማት ሊሰጠው የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
3. የመንግስት ሰራተኛ በመስክ ስራ ላይ እያለ ድንገተኛ ጉዳት ሲያጋጥመው በአካባቢው በቅርበት በሚገኝ ህጋዊ እውቅና ባለው ማንኛውም የህክምና ተቋም እንዲታከም በማድረግ ወጪውም በሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ ይሸፈናል፡፡
4. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ ድንገተኛ ጉዳት ሲያጋጥመው መስሪያ ቤቱ በአካባቢው በቅርበት በሚገኝ ህጋዊ እውቅና ባለው ማንኛውም የህክምና ተቋም በራሱ ማጓጓዣ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን መስሪያ ቤቱ አገልግሎቱን ማቅረብ ካልቻለ ሰራተኛው ለትራንስፖርት ላወጣው ወጪ የሚያቀርበውን ማስረጃ ከሀገሩ የትራንስፖርት ታሪፍ ጋር በማነፃፀር እና በማረጋገጥ ወጪውን ይሸፍናል፡፡ ከተረጋገጠው ታሪፍ በላይ የሚገልፅ መረጃ ቢያቀርብ ተጨማሪውን ወጪ ሰራተኛው እራሱ ይሸፍናል፡፡
5. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ጉዳት ሲደርስበት ወጪውን በቀጥታ መክፈል የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም መስሪያ ቤቱ የዱቤ ህክምና እንዲያገኝ ከህክምና ተቋሙ ጋር በመነጋገር እርዳታውን የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
6. የስራ ባህሪያቸው ለኬሚካል፣ ለጨረር፣ ለብናኝና ለከፍተኛ ሽታ በሚያጋልጡ የስራ መደቦች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ ሰራተኞች ጤንነታቸውን ለመጠበቅ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ

ቤተሰብ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

መሰረት በመንግስት የሕክምና ተቋም ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ የጤና ምርመራ እንዲያገኙ ከአንድ የመንግስት የህክምና ተቋም ጋር ይዋዋላል።

7. የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 53 ንኡስ አንቀፅ (2) (ሐ) በተደነገገው መሰረት የመንግሥት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው መንግስት ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም መስሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልፅ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ በመንግስት ሰራተኛው ላይ ለሚደርስ ጉዳት በዚህ መመሪያ መሰረት የህክምና ወጪው እንዲሸፈን ያደርጋል።

## 8. የህክምና ምርመራና የመድሐኒት ግዢ አፈፃፀም

በስራ ላይ ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ሰራተኛ ምርመራና የመድሀኒት ግዢ በሐኪም ሲታዘዝ አገልግሎቱ በመንግስት የህክምና ተቋም አለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ከግል የህክምና ተቋምና ፋርማሲዎች ምርመራውን በማድረግ ወይም ግዢ በመፈጸም በሚያቀርበው ደረሰኝ መሰረት ወጪው በመስሪያ ቤቱ እንዲሸፈን ይደረጋል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

## ክፍል ሶስት

### 9. የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት

1. የመንግስት ሰራተኞች በስራ ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የመከላከያ ዘዴዎችን ተግባራዊ የማድረግ፤
2. ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ ህይወትን ለማትረፍና ዘላቂ ጉዳት እንዳያስከትል የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ የሚሰጥበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
3. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ጉዳት ስለመድረሱ እና ተገቢውን ህክምና ማግኘቱን የሚቀርቡ መረጃዎችን በስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ ወይም በሚመለከተው አካል የማረጋገጥ፣
4. የሕክምና ወጪ የሚሸፈንበትን በጀት ማስመደብ ወይም የጤና መድህን መግባት፣
5. በስራ ቦታ ላይ ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው አካላት በስራ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የህክምና ወጪን በተመለከተ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲተገበሩ ግንዛቤ የመፍጠር፤
6. ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰጡር ሴቶች እና የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝባቸው ሰራተኞች ከስራ ጋር በተያያዘ ለጉዳት እንዳይዳረጉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት፣
7. የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ ማቅረብ፣ ስለአጠቃቀሙ ሥልጠና መስጠት እና በትክክል የሚሰሩ መሆኑን የመከታተል፣
8. የመንግስት ሰራተኛውን በተደጋጋሚ ለጉዳት የሚያጋልጥ የስራ ባህርይን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ የመውሰድ፣
9. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ የማድረግ፤
10. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ ጉዳት ደርሶበት በራሱ ወጪ ህክምና ካደረገ ያወጣውን ወጪ እንዲመለስለት ተገቢውን ማስረጃ አሟልቶ፣ ጥያቄው በቀረበ 10 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የመክፈል፣
11. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ በተሰጠው ህክምና ምክንያት ተጨማሪ የጤና መቃወስ ካልደረሰበት በስተቀር በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ በአግባቡ አለመፈፀሙ በሐኪሙ ከተረጋገጠ የሚሰጠው ህክምና እና የህመም ፈቃዱ እንዲቋረጥ የማድረግ ፣
12. በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው ህይወቱ ቢያልፍ የህክምና ወጪውን ለህጋዊ ወራሹ የመክፈል፣ አስክሬኑን ወደ ቤተሰቦቹ ለማድረስ በመስሪያ ቤቱ ተሸከርካሪ

እንዲመደብ የማድረግ ወይም ለዚሁ ጉዳይ የሚያስፈልገውን ወይም የወጣውን ወጪ የመሸፈን እንዲሁም በአዋጁ አንቀፅ 60 ላይ የተደነገጉት መብቶቹ እንዲጠበቁለት የማድረግ፣

ተግባርና ኃላፊነት አለበት።

## 10. የመንግስት ሰራተኛው መብት

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፣

1. ለስራው የሚያስፈልገውንና የተፈቀደለትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያና ቁሳቁስ የማግኘት፣
2. በስራ ምክንያት ጉዳት ከደረሰበት ህክምና እንዲደረግለት የመጠየቅና የማግኘት፣
3. ለበሽታ የሚያጋልጥ የስራ መደብ ላይ ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ በአመት ሁለት ጊዜ የጤና ምርመራ የማግኘት፣

መብት አለው።

## 11. የመንግስት ሰራተኛው ግዴታ

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፣

1. ለስራው የተሰጠውን የአደጋ መከላከያ መሳሪያና ቁሳቁስ በአግባቡ የመጠቀም፣
2. በስራ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት የወሰደውን የህክምናና የመድሃኒት ወጪ ህጋዊ ማስረጃ የማቅረብ፣
3. የህክምና ማስረጃውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ህክምናውን እንደጨረሰ የማቅረብ ፣
4. በስራ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት የሐኪም ትዕዛዛትን ተከትሎ ህክምናውን በአግባቡ የመከታተል፣
5. በመደበኛ ስራም ሆነ በመስክ ስራ ላይ እያለ በራሱ ላይም ሆነ በሌሎች ሰራተኞች ላይ ለጉዳት ሊያጋልጥ የሚችል ክስተት መኖሩን ሲመለከት ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

ግዴታ አለበት።

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. ተጠያቂነት

1. ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ አግባብነት የሌለው የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ያቀረበውን ሰራተኛ በወንጀል የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ከሕግ ውጭ ለሚፈጽማቸው ተግባራት ሁሉ በአዋጁ አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ኮሚሽኑ ይህንን መመሪያ በተገቢው ሁኔታ በማይተገብሩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

### 13. የቅሬታ አቀራረብ

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ያለው ከሆነ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት በደንብ ቁጥር 77/1994 መሰረት ቅሬታውን በማቅረብ ምላሽ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

### 14. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 15. መመሪያውን ስለማሻሻል

ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 16. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኮሚሽነር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር